ግብርና ሚኒስቴር

ኳራንቲን ኢምፖርት ኤክስፖርት ኢንስፔክሽንና ሰርተፍኬሽን ዳይሬክቶሬት

Ministry of Agriculture

Quarantine Import Export Inspection Certification Directorate

## *ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ ውሻ እና ድመት ማስገቢያ ፍቃድ ለማግኘት የሚያስፈልጉ ሰነዶች*

- የቤት እንስሳውን (ውሻ/ድመት) የማስገቢያ ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ
- ከአንድ ወር ያላነሰ ከአመት ያልበለጠ የእብድ ውሻ በሽታ ክትባት የተሰጠበት ክትባት ሰነድ
- ከላኪ ሀገር መንግስት የተሰጠ የመውጫ ፍቃድ
- ከተመዘገበ የግል ሀኪም የሰጠ አጠቃላይ የጤና ማረጋገጫ

***Requirements for Pet Import permit***

- Signed application request for entry
- Copy of vaccination card with full current vaccinations and full pet details
- Export permit from the competent Gov. authority of the exporting country
- Rabies vaccination must have been given within a year and no less than a month.
- Copy of the owner’s/consignee’s passport

## *ድመትና ውሻ ከኢትዮጵያ ወደ ውጪ ይዞ ለመውጣት የሚያፈልጉ ሰነዶች*

- የመውጫ ፍቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ ማቅረብ
- የእብድ በሽታ ክትባት ከአንድ ወር ያላነሰ ከአመት ያልበለጠ የተሰጠበት ክትባት ሰነድ
- በደም ውስጥ ያለ የእብድ ውሻ በሽታ መከላከያ ሰነድ
- ከእውቅና ካለው የግል የእንስሳት ክሊኒክ የተሰጠ ጠቅላላ ጤና ማረጋገጫ ሰርተፍኬት

***Requirements for Pet export permit***

- Signed application for export permit
- Copy of vaccination card with full current vaccination and full pet details
- General health certificate from a registered Veterinary clinic
- Rabies vaccination must have been given within a year and no less than a month.
- Copy of the owner’s/consignee’s passport
- Rabies antibody titration record for Europe export
- Other diagnostic tests based on the importing country requirement

ግብርና ሚኒስቴር

<u>ኳራንቲን ኢምፖርት ኤክስፖርት ኢንስፔክሽንና ሰርተፍኬሽን ዳይሬክቶሬት</u>

Ministry of Agriculture

<u>Quarantine Import Export Inspection Certification Directorate</u>

## *ማር ወደ ውጪ ሀገር ለመላክ ማምረቻ ቦታው መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች*

- ዙሪያው የታጠረ የማር ማቀነባበሪያ /ማዘጋጃው ቤት የግል ከሆነ ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ፕላን አሊያም የኪራይ ከሆነ በውልና ማስረጃ የተረጋገጠ የኪራይ ውል ማቀረብ የገባል
- የቤቱ ጣሪያ፤ግድግዳና ኮርኒስ (አይጥ፤ድመት ፤አእዋፍትና ሌሎችም) እንስሳትን እንዳያስገባ ቀዳዳ የሌለው መሆን አለበት
- የቤቱ ወለልና ግድግዳ በውሃ ሊታጠብ የሚችል መሆን አለበት
- የሰራተኞች ልብስና ጫማ መቀየሪያ፤መፀዳጃና መታጠቢያ ክፍሎች ሊኖረው ያስፈልጋል
- በቂ የሆነ ለመጠጥነት የሚውል ውሃ መኖር አለበት
- የማር ማቀነባበሪያ ቦታ በአቅራቢያው ኬሚካል የሚየመርቱ ፋብሪካዎች፤ጭስ የሚለቁ ፋብሪካዎች ወይም ማርን ሊበርዙና ሊበክሉ የሚችሉ ፋብሪካዎች ሊኖሩ አይገባም (ማር በተፈጥሮው ሽታ ስለሚስብ)
- ለሰራተኞች የሚያገለግሉ አልባሳትና ጫማዎች በየጊዜው እየጸዱ በተለየ ክፍል ውስጥ ተዘጋጅቶ መቀመጥ ይኖርበታል
- ለጎብኚዎች የሚያገለግሉ አልባሳትና ጫማዎች በየጊዜው እየጸዱ በተለየ ክፍል ውስጥ ተዘጋጅቶ መቀመጥ ይኖርበታል
- የሰራተኞች የ3 ወር ወይም የ6 ወር የጤና ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ሊኖር የገባል
- ማር የሚቀመጥባቸው ኮንቴነሮች ወይም ማሸጊያዎች ንጽህናቸው የተጠበቀና ለማር ደህንነት ሲባል ከተከለከሉ ማቴሪያሎች (ኮፐር፤ዚንክ ፤አይረን፤ ሊድ እና ሌሎችም)ያልተሰሩ ወይም ያልተነካኩ ሊሆኑ ይገባል
- ማር የተቀመጠባቸው ኮንቴነሮች ወይም እሽጎች የመቀደድ አደጋ ቢያጋጥም በሰም መድፈንና መለሰን ወይም በተመሳሳይ ለማር ደህንነት ሲባል በተፈቀዱ መድፈኛዎች አሊያም መለሰኛዎችን መጠቀም ያስፈልጋል

## የጤና ሰርተፍኬት ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

- የጤና ሰርተፍኬት መጠየቂያ ቅጽ ማቅረብ
- የባንክ ፐርሚትና ፕሮፎርማ ኢንቮይስ
- በተቆጣጣሪው መ/ቤት በኩል ወካይ ናሙና መውሰድ
- ምርቱን በማሸግ በኢትዮጵያ ተስማሚነት እና ምዘና ወይም አውሮፓ ዕውቅና ባለው የላቦራቶሪ ፍተሻ ተደርጎ የጥራት እና ደህንነት ደረጃው ማረጋገጥ

**ኢንስፔክሽን የሚያካሂደውን ባለሙያ የሚያከናውናቸው ተግባራት**

- የቤቱን ንፅህና (የሸረሪት ድር፤በራሪ ነፍሳቶች፤አይጥ፤ወፎች፤የተቀደደ ጣሪያ፤ኮረኒስ፤ግድግዳ እና ወለል፤የቆሸሸ ጣሪያ፤ኮረኒስ፤ግድግዳ እና ወለል) መመልከት
- የሰራተኞቹን ንፅህናና አለባበስ (ንፁህና ለስራ ሰአት ብቻ የሚለበስ ልብስ መሆኑን እንዲሁም ሁሉም ሰራተኞ በስራ ላይ ከሆኑ ፀጉራቸውን በሚገባ ሊሸፍኑ ይገባል
- የማር ማቀነባበሪያና ማሸጊያ አቃዎችን ንፅህና (ያልዛጉ፤ጋልቫናይዝድ ያልሆኑ፤ያልቆሸሹ፤ያልተሰበሩ መሆነቸውን) እና ለማር ደህንነት ሲባል ከተከለከሉ ማቴሪያሎች (ኮፐር፤ዚንክ ፤አይረን እና ሊድ) ያልተሰሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ
- የማሩን ጠረን፤ጣዕም፤ከለርና ይዘት መገምገም
- ማር የያዘው እቃ/ኮንቴነር በአግባቡ የተከደነና የተለበጠ (ሲልድ) የሆነ መሆኑን ማረጋገጥ
- ማር የያዘው እቃ/ኮንቴነር ጎኑ ላይ ወይም አመቺ በሆነ ቦታ ላይ የሚከተሉት ዝርዝሮች መኖራቸውን ማረጋገጥ
- ማሩን ያዘጋጀው ድርጅት ስምና አድራሻ
- የተጣራ ክብደቱ
- ለምግብነት የማብቂያው ቀንና ዓ.ም
- የተመረተበት ሀገር ስም

**ግብርና ሚኒስቴር**

Ministry of Agriculture

ኳራንቲን ኢምፖርት ኤክስፖርት ኢንስፔክሽንና ሰርተፍኬሽን ዳይሬክቶሬት

Quarantine Import Export Inspection Certification Directorate